የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)
Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ህዳር 21ቀን 2001 ዓም

# የዓለም አቀፍ ኤይድሰ ቀንን አስመልክቶ የወጣ መግለጫ

በዓለም አቀፍ ደረጃ የኤይድስ ቀን ሲከበር በሀገራችን ኢትዮጵያ ይህ ቀሳፊ በሽታ በወያኔ አገዛዝ ፖሊሲዎች እየታገዘ በመስፋፋት ላይ መሆኑ መጋለጥ ያለበት ሀቅ ነው። በሽታውን በቁጥጥር ስር አስገባሁ ብሎ እየተመፃደቀ ያለው አገዛዝ ዋና ዋና ባለሥልጣኖቹን ሳይቀር ለዚሁ በሽታ አሳልፎ ከመስጠቱ ሌላ በሀገሪቷ ላይ ያመጣው የኤኮኖሚ ክስረት ማህበረሰባዊ ቀውስ ለዚህ በሽታ መስፋፋት ዋና ምክንያት ሆኗል።

ወያኔ ለሥልጣን ሲበቃ ኤይድስን ከመቆጣጠር አንፃር ተመስርቶ ይሰራ የነበረውን ተቋም አፈረሰ። በወታደሮቹ አማካይነትም በሽታውን በየቦታው አሰራጨ። ኤይድስን መዋጋት በሚልም የአምባገነኑ ባለቤት፣ አቡን ተብዬውና ሌሎች ባለሥልጣኖች የእርዳታ ገንዘብ መዘበሩ። በተጨባጭ ግን በቀን በዚህ በሽታ የሚለከፈውና የሚሞተው ሰው ቁጥር ባለፉት አራት ዓመታት ጨመረ እንጅ አልቀነሰም። በሽታው በተለይ በገጠር እየተስፋፋና በብዛትም ሴቶችን እያጠቃ ነው። በኤይድስ የተነሳ ቤተሰብ አልባ የሆኑ ህፃናት ቁጥር አንድ ሚሊዮንን ካለፈ አራት ዓመት ሆኖታል። መንገድ አዳሪ ወጣቶች ለዝሙት እየተጋለጡና እየተደፈሩ፣ ሥራ አጥነት ተስፋፍቶና ቀቢፀ ተስፋ አይሎ፣ አልባሌ ልምዶች ሲስፋፉ፣ አደንዛዥ ዕፆችን የአገዛዙ ባለሥልጣኖች ሳይቀር ሲነግዱ፣ ወጣቱ ለበሽታው እንዲጋለጥ ሲገፋፋና የሀገሪቷም የጤና ጥበቃ ተቋም ፍልስሰልሱ ወጥቶ ከቀን ወደ ቀን ኤይድስ አያሌ ዜጋን እየበከለና ከወባ ተደምሮ ብዙ ህይወትን እያጠፋ ነው። በአፋዊ ደረጃ አገዛዙ የተቀረቀረ መስሎ ለመቅረብ ቢሞክርም የህዝብን ጤና ከመጠበቅ አንፃር ደንታ የሌለው ቡድን መሆኑ የሚታወቅ ነው። በኤይድስ በሽታ የተነሳ ሀገራችን  በተለይ ሴቶች ልጆቿን እያጣች ነው። አምራቹ የሰው ኃይል እየተጠቃ ነው። ወጣቱ እየተጠቃ ነው። የኤኮኖሚው ድቀት፥ ድህነትና ፍትህ አልባ ሁኔታ በመስፈኑም ዜጎች ራሳቸውን ከአደጋ የሚጠብቁበት አቅምም ፍላጎትም እንዲያጡ እየተደረገ ነው።

ኢሕአፓ የወያኔ አገዛዝ በዚህ መስክ በሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለውን ጥቃት እያወገዘ ዜጎች በተቻላቸው ደረጃና መጠን ሁሉ ራሳቸውን እንዲጠብቁና ለዚህ ቀሳፊ በሽታ ሰለባ እንዳይሆኑ ማሳሰቡን ይቀጥላል። በበሽታው የተያዙትንም በዜጋ ፍቅር መንከባከብና መርዳት ግዴታ መሆኑ መዘንጋት የለበትም።

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com

Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France